BIG HOUSING BUILD

Amharic | አማርኛ

# በፍሌሚንግተን የሚከናወኑ የወደፊት ሥራዎች

የስራ ማስታወቂያ

ጁላይ 2026

homes victoria

## የመሠረተ ልማት እና የመገልገያ ስራዎችን ለመቀጠል የስራ በታውን ማስፋት

### ከኦገስት እስከ ኖቬምበር

በአከባቢው የሚገነቡ አዳዲስ ቤቶች የወደፊት ልማት ለመደገፍ የመሠረተ ልማት እና የመገልገያ ስራዎች በመካሄድ ላይ ናቸው ደግሞም እስከ 2026 መጨረሻ ድረስ ይቀጥላሉ።

### ምን እንደምንሰራ

- የመሠረተ ልማት እና የመገልገያ ስራዎችን መትከል ለመቀጠል የስራ በታውን ወደ ደቡብ ወደ ሬስኮርስ ሮድ ማስፋፋት
- በ120 ሬስኮርስ ሮድ/Racecourse Road እና በ12 ሆላንድ ኮርት/Holland Court መካከል ወደ መኪና ማቆሚያ የሚመሩ የመግቢያ እና መውጫ ነጥቦችን መቀየር
- የአምቡላንስ መቆሚያ እና የማውረጃ ዞን ወደ ሌላ በታ ማዛወር
- በ120 ሬስኮርስ ሮድ እና በ12 ሆላንድ ኮርት መካከል ባለው የመኪና ማቆሚያ በታ ላይ የመሬት ምርመር ስራ ይሰራል። በእነዚህ ስራዎች ወቅት የመኪና ማቆሚያው ክፍት ሆኖ ይቆያል
- የሥራ በታዎችን መቆፈር እና በአፈር መሙላት
- አንዳንድ ዛፎችን እና እፅዋትን ማስወገድ
- በበታው ላይ ከተገኙ አደገኛ ቁሳቁሶችን ማስወገድ።

ደህንነትን ለማረጋገጥ እና መስተጓጎልን ለመቀነስ ሁሉም ስራዎች ባሉት ፕሮቶኮሎች መሰረት ይጠናቀቃሉ።

### ምን እንደሚጠበቅ

- በመኪና ማቆሚያ በታዎች፣ በመኪና ማቆሚያ መግቢያዎች እና በግቢው ዙሪያ ባሉ የእግረኛ መንገዶች ላይ በመካሄድ ላይ ያሉ ለውጦች። እባክዎ የትራፊክ አስተዳደርን እና ምልክቶችን ይከተሉ
- በኦገስት ወር መጨረሻ ላይ በ130 ሬስኮርስ ሮድ እና በ12 ሆላንድ ኮርት አቅራቢያ የመኪና መቆሚያዎች በየደረጃው እንደገና ይከፈታሉ
- ወደ ሬስኮርስ ሮድ የሚያወጣው የመውጫ መስመር አንዳንድ ጊዜ ለጊዜው መዘጋት። በዚህ ወቅት የተሽከርካሪ መዳረሻ ምልክት በተደረገበት መስቀለኛ መንገድ ላይ ይኖራል

More Homes For Victorians

VICTORIA State Government

- በግቢው ውስጥ የስራ ቦታዎችን እንደገና በየደረጃው መከፈት
- በስራ ጊዜ የሚኖር ጫጫታ እና ንዝረት
- በግቢው ውስጥ መደበኛ የጭነት መኪና እና የተሽከርካሪ እንቅስቃሴዎች
- እንደ አስፈላጊነቱ ነጭ የደህንነት ልብሶችን ጨምሮ የግል መከላከያ መሳሪያዎች የለበሱ ሰራተኞች ይኖራሉ።

## ደህንነትዎን መጠበቅ እና የግንባታ ተፅእኖዎችን መቀነስ

- ወደ 130 ሬስኮርስ ሮድ የሚወስድ አዲስ አማራጭ የእግረኛ መዳረሻ አሁን በአዲሱ የህዝብ መናፈሻ (ሙርናሉንግ ፓርክ) በኩል ተከፍቷል
- በስራ ዞኖች አቅራቢያ በሚሰሩ ስራዎች ወቅት ጫጫታ፣ ንዝረት እና የአየር ጥራትን መከታተል
- በግቢው ዙሪያ የስራ ቦታ ምልክቶችን መትከል
- እንደ አስፈላጊነቱ ተሽከርካሪዎችን እና እግረኞችን ለመምራት በስራ ዞኖች አቅራቢያ የተመደቡ የትራፊክ ተቆጣጣሪዎች
- የቆሻሻ ማጠራቀሚያ መሰብሰቢያ እና የአደጋ ጊዜ መውጫ መንገዶች እንዳሉ በቦታቸው ይቆያሉ።

## የስራ ሰዓቶች

ስራዎቻችን የሚመሩት በምክር ቤቱ መደበኛ የስራ ሰዓት ነው፡-

**ከሰኞ እስከ አርብ**
ከጠዋቱ 7 ሰዓት እስከ ምሽቱ 6 ሰዓት ባለው ጊዜ ውስጥ

**ቅዳሜ**
ከጠዋቱ 9 ሰዓት እስከ ከሰዓት በኋላ 3 ሰዓት ባለው ጊዜ ውስጥ

## ስለ ትዕግስትዎ እናመሰግናለን

እነዚህን አስፈላጊ ስራዎች በምናከናውንበት ወቅት ስለ ትዕግስትዎ እናመሰግናለን።

### ስለ ሥራዎቹ ጥያቄ አለዎት?

ስለእነዚህ የታቀዱ ስራዎች ማንኛቸውም ጥያቄዎች ካሉዎት ወይም አስተርጓሚ ከፈለጉ እባክዎን በ flemington@homes.vic.gov.au ኢሜል ይላኩልን።

## የስራ ቦታ ካርታ




## ለተጨማሪ መረጃ

ስለ ሆምስ ቪክቶሪያ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት እባክዎ ወደሚከተለው ይሂዱ፡- homes.vic.gov.au

በቪክቶሪያ መንግስት የተፈቀደ እና የታተመ፣ 1 Treasury Place, Melbourne። © የቪክቶሪያ ግዛት፣ አውስትራሊያ፣ ሆምስ ቪክቶሪያ፣ ጁላይ 2026።

More Homes For Victorians
VICTORIA State Government